ራሺዳ ቤህቡዶቫ

# ረሺድ ቤይቢቶቭ - የአዘርባጃን እና የኢትዮጵያ የባህል ግንኙነት መስራች

የዕውቅናው ጣሪያ ጫፍ በደረሰበት በ1959 እ.አ.አ የበልግ ወራት ረሺድ ቤይቢቶቭ ወደ ተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት በርካታ ጉብኝቶችን ለማድረግ ወደ አህጉሪቱ አቀና፡፡ በጉብኝቱ ከሩሲያ፣ ዩክሬን፣ ኡዝቤኪስታን፣ ላቲቪያ እና ከሌሎች የሪፐብሊክ ግዛቶች የተወጣጡ በዓለም ዙሪያ ታዋቂ የነበሩ የሶቭየት አርቲስቶች ልዑካን ቡድን መሪ ነበር፡




ET-
ETHIOPIAN
FLIGHT
609
ETHIOPIAN



፡ በእርግጥም እንደዚያ ዕውቅናቸው የናኘ የአርቲስቶች ቡድን መሪ የነበረ መሆኑ ምን ያህል የገዘፈ ስም እንደነበረው የሚመሰክር ሀቅ ነው፡፡ በኢትዮጵያ፣ ሱዳን እና ሊቢያ ያደረገው ጉብኝት ወደ አንድ ወር ከግማሽ ያህል የፈጀ ነበር፡፡ በጉዞው ወቅት 26 የሙዚቃ ትዕይንት መድረኮች (ኮንሰርቶች) ለህዝብ ለማቅረብ በቅቷል፡፡ እነዚህ ስመ ጥር አርቲስቶች በኢትዮጵያ እና በቀሪው የአህጉሪቱ ክፍላት ከፍተኛ በሆነ ደረጃ የሞቀ አቀባበል ተደርጎላቸው ነበር፡፡ በጉብኝቱ ቀጣይ ቀናት በተለያዩ አዳራሾች በርካታ ኮንሰርቶች ቀርበው ነበር፡፡ ከኮንሰርቶቹ መሀል አንደኛው ኮንሰርት የቀረበው "የማይነጥፍ ምንጭ መዲና" ተብላ በምትጠራው የኢትየጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ በሚገኘው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር ነበር፡፡ በንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ የሚመራው የሀገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ስብስብ የዝግጅቱ ታዳሚ ነበር፡፡ በዚህ ኮንሰር ወቅት ረሺድ ቤይቢቶቭ ባደረገው ንግግር ታዳሚውን በሚደንቅ ሁኔታ ለማስደመም ችሎ ነበር፡፡

በመድረኩ ባቀረበው ስራ ተማርከው የነበሩት ተመልካቾች ከመድረኩ በቀላሉ እንዲወርድ ፈቃዳቸው አልነበረም፡፡ የፊከርት አሚሮቭ፣ ቶፊግ ኩሊዬቭ ሰይድ ሩስታሞቭ እና የአዘርባጃንን ባህላዊ ዘፈኖች አፍ በሚያስከፍት ችሎታ ውብ አድርጎ ተጫወተ፡፡ አስገራሚው ነገር ከዘፈኑ ግጥም እና አዝማች በኋላ ታዳሚው የተወዳጁን ሙዚቀኛ ዘፈን አዝማች በአንድ ላይ የመዝፈናቸው ክስተት ነበር፡፡

"አልማዜ" የሚለውን የኢትዮጵያን ባህላዊ ዘፈን በጥንታዊው የአማርኛ ቋንቋ ማዜም ሲጀምር መላው አዳራሽ በስሜት ተናጠ፡፡ ታዳሚው ከመቀመጫው ተነስቶ በአድናቆት ያለማቋራጥ በጭብጨባ አድናቆቱን ገለፀ፡፡ ቤይቡቶቭ "አልማዜ" የሚለውን ሙዚቃ ብዙዎች ምናልባት ኢትዮጵያዊ የዘር ግንድ ሳይኖር አይቀርም ብለው እስኪጠራጠሩ ድረስ በአስደናቂ ችሎታ ለመጫወት ችሎ ነበር፡፡ኮንሰርቱ ካበቃ በኋላ ብዙዎች እየቀረቡት ኢትዮጵያዊ



ዘር ያለው መሆኑን ይጠይቁት ነበር፡፡ ከዝግጅቱ በኋላ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ለራሺድ ቤይቡቶቭ ክብር ባዘጋጁት ግብዣ ወቅት ንጉሠ ነገሥቱ ሙዚቀኛው የዘር ግንዱ ከየት እንደሆነ ጠይቀውት ነበር፡ እኚህ ታላቅ ንጉሠ ነገሥት ባህላዊ የሆነውን “አልማዜ” የተሰኘውን ሙዚቃ በትክክለኛ አማርኛ ቃና እና ቅላጼ መዝፈኑ እጅግ እንግዳ እና አስገራሚ ሆኖባቸው ነበር፡፡ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ሌሎቹ የሙዚቃ ቡድኑ አባላት የራሺድ ቤይቡቶቭ ባህላዊ ሙዚቃ አጨዋወት አርአያ እንዲሆናቸው በመናገር ለአርቲስቱ የኢትዮጲያን የወርቅ ኒሻን ሸልመውታል፡፡

በአጠቃላይ በራሺድ ቤይቡቶቭ ህይወት የዘር ግንዱ የተጠየቀበት አጋጣሚ ይህ አጋጣማ ብቻ አልነበረም፡፡ ይህ አስገራሚ እና አንግዳ የሆነው የአርቲስቱ ችሎታ በቻይና፣ በህንድ እና በሌሎች በርካታ ሀገራት ተመሳሳይ ጥያቄ አንዲጠየቅ ምክንያት ሆኗል፡፡ የዚህ የአርሰቲስቱ ከህሎት ሚስጥር አርሰቲስቱ የሚዘፍናቸውን ሁሉም ዘፈኖች በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት፣ አክብሮት እና ትኩረት ስለሚያቀነቅናቸው እና ለስራው ያለውን ሙሉ ችሎታ ሁሉ የሚያውል መሆኑ ነበር፡፡ ራሺድ ቤይቡቶቭ በጎበኘው እያንዳንዱ ሀገር የየሀገሩን ባህላዊ ሙዚቃ መጫወት ለእርሱ ግድ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ለሌሎች ሀገራት አርሰቲስቶች አርዓያ እንዲሆን አስችሎታል፡ ፡ ይህ ታላቅ አርሰቲስት የሚያጠናው የሚጫወተውን ሙዚቃ የቋንቋ የድምጽ አወጣጥ እና ቃላት ብቻ ሳይሆን የሙዚቃ ስራውን ለሚያቀርብለት ህዝብ ውስብስብ የሙዚቃ እንደምንታ ጭምር ነበር፡፡ ይህም በመሆኑ ራሺድ ቤይቡቶቭ ያዜማቸው ሙዚቃዎች በሙሉ የአድማጩን ነፍስ ጥልቅ በሆነ መልኩ የመንካት አቅም ሊኖራቸው ችሏል፡፡ ወደ ኢትዮያ ያደረገው ጉዞ በደማቅነቱ ለረዥም ጊዜ ሲታወስ ኖሯል፡፡ ልክ የዛሬ 60 ዓመት በአዘርባጃን እና በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል የባህል ድልድይ ለመዘርጋት ሊበቃ ችሏል፡፡

ራሺድ ረሺድ እና ካሚል ሻሽርዲ